# ይልቅስ ጣልቃ ገብነትን እናውግዝ!

ከመሃመድ ጀማል

የኢትዮጵያ ጠቅላይ የሸሪአ ፍርድ ቤት የሶማሊያን ዋና ከተማና አብዛኛውን የሃገሪቱ ደቡባዊ ግዛት የተቆጣጠረውን የሶማሊያ ኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ማውገዙን የሚገልጽ ዜና ሳነብ ከመነሻው ያሳቀኝ ቢሆንም ማሳዘኑና ማሳፈሩ ግን አልቀረም። ይህ የሸሪአ ፍርድ ቤት ተብየው የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን በተለይም ድሆች፣ ረዳት አልባና ጉቦ ለመስጠት አቅማቸው የምይፈቅድላቸው ምስኪኖችን በማስለቀስና በማሸበር ወደር የማይገኝለት የአላህ ፍራቻ የሚባል ነገር ባጠገባቸው ባላለፈ ወሮበሎች የተሞላ ድርጅት ነው። አላህ በዘመድ መስራትን፣ ማዳላትናን ጉቦ መብላትን የሚጠላ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም እነኝህ በአላህ ስም እንፈርዳለን በማለት ፍርድ ቤቱን የሞሉት ግለሰቦች የተዘረጠጠ ቀፈታቸውን የሞሉት በድሃው ሙስሊም እንባና በጉቦ መሆኑ የአደባባይ ሚስጢር ነው። እነኝህ የሙስሊሙ ኡማ በአላህ ህግ መዳኘትን እንፈልጋለን በማለት በብርቱ ትግል እንዲቋቋም ያደረገውን ፍርድ ቤት በጉቦና በአድልኦ ስራ ያራከሱ ናቸው። እንደ እነኝህ ያሉ ሙእሚኑ ከአላህ እንዲሸሸ የሚያደርጉ ክፉዎች ስለ ሌላ ቡድን አሸባሪና የመሳሰሉትን ቅጽል ስሞች እያወጡ ለመናገር የሚይበቃ ምን አይነት ሞራላዊ ብቃት አላቸው?

የኢትዮጵያ ጠቅላይ የሸሪአ ፍርድ ቤት የሚሰጠውን መግለጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ከቁምነገር እንደማይቆጥረው የሸሪአ ፍርድ ቤቱም ሆነ መንግስት በሚገባ ያውቁታል። የሸሪአ ፍርድ ቤቱ ውስጥም ሆነ መጅሊሰል አእላ በሃላፊነት የተቀመጡት ሰዎች በስራ ብቃታቸውና በህዝብ ምርጫ ሳይሆን የግል ጥቅሞቻቸውን የሚያስቀድሙና በሙስና የተዘፈቁ ወንጀለኞች በመሆናቸው ነው። እንድ ኢትዮጵያ መንግስት ያሉ በህዝብ ፍላጎትና ምርጫ ሳይሆን በጎልበት የተቀመጡ መንግስታት ለመገልገያነት የሚመርጧቸው ሰዎች ህዝብን ለማገልገል የቆሙ፣ ለህዝብ ጥቅም ቅድሚያን የሚሰጡና ለቆሙለት መርህ ጽኑዎች የሆኑ ግለሰቦችን ሳይሆን ራስ ወዳዶች በመሆናቸው የተነሳ በቀላሉ በጥቅም የሚገዙ ሰዎችን እንደሆነ የታወቀ ነገር ነው። የሸሪአ ፍርድ ቤቱ ውስጥም ሆነ መጅሊሰል አእላ በሃላፊነት የተቀመጡት ሰዎች የተመለመሉት በዚህ ከላይ በጠቀስነው መርህ መሰረት ስለሆነ በህዝብ ዘንድ ምንም አይነት አመኔታ እንደሌላቸው እነርሱም መንግስትም ጠንቅቀው ያውቃሉ። መንግስት መጅሊሱንም ሆነ የሸሪዓ ፍርድ ቤቱን የሶማሊያን ኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረትን እንዲያወግዙ ትእዛዝ ሲሰጥ የኢትዮጵያ ሙስሊም ህብረተሰብ ከጎኔ እንዲሰለፍ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ በሚል ተስፋ አይደለም።

የኢትዮጵያ መንግስት ቅስቀሳ ያነጣጠረው በአንድ በኩል በምዕራቡ አለም ላይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ከወንድሞቻቸው ከሶማሊያውያን ሙስሊሞች ጋር ለማናከስ ታስቦ ነው። መጅሊሱንና የሸሪዓ ፍርድ ቤቱን ፀረ ሶማሊያ የሆነ መግለጫ እንዲሰጡ በማድረግ መንግስት በአንድ በኩል ለምዕራቡ አለም “ተመልከቱ የሀገሬ ሙስሊሞች ከጎኔ ቆመዋል“ የሚል መልዕክት ሲያስተላልፍ በሌላ በኩል ፤ በእኔ አመለካከት በጣም አደገኛ የሆነው ዓላማ ደግሞ የኢትዮጵያውያን

ሙስሊሞችን ፍላጎት በምንም አይነት መልኩ የማይወክሉ ግለሰቦች በስሙ ፀረ ሶማሊያ የሆኑ መግለጫዎችን እንዲሰጡ በማድረግ ወንድማማች በሆኑት በሁለቱ ሃገራት ሙስሊሞች መካከል ጥላቻን መፍጠር ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት የራሱን የአገዛዝ እድሜ ለማራዘም ሲል የሶማሊያው የኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት አሸባሪ ነው ፣ የአል ቃዒዳ አካል ነው፣ በኢትዮጵያ ላይ ጂሃድ አውጇልና ወዘተ እያለ በአሉባልታ ላይ የተመሰረተ የቅስቀሳ ዘመቻውን በሰፊው ተያይዞታል። የኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት አሸባሪ ስለመሆኑ ወይንም እንደ አል ቃዒዳ ከመሳሰሉ ድርጅቶች ጋር አለው እያለ ስለሚለፍፈው የፈጠራ ወሬ አንዲትም እንኳን መረጃ ማቅረብ አልቻለም። የኢስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ያወጀው ነገር ቢኖር የመከላከል እርምጃ ነው። አንድ ሃገር ደንበሩ በውጪ ወራሪ ሀይል ሲደፈር የመከላከል መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለበት።

የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያ ውስጥ ምን ያደርጋል? የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ የሚፈተፍትበት ምክንያት ምንድነው? እርሱ እንደሚለው የኢትዮጵያን ብሄራዊ ደህንነት ለመጠበቅ ነው?

ሶማሊያ ጎረቤት እንደመሆኗ መጠን እውስጧ የሚከሰቱ ጉዳዮች ሊያሳስቡን ይገባል። በተለይ በአሁን የደህንነት ፅንሰ ሃሳብ እየሰፋ መጥቶ የአየር ብክለት እንኳን እንደ የደህንነት ጥያቄ በተወሰደበት ዘመን እዚሁ አፍንጫችን ሥር የሚካሄድ የእርስ በርስ ግጭት በደህንነታችን ላይ አደምታ አይኖረውም ለማለት አይቻልም። ስለዚህ ኢትዮጵያ በሶማሊያ ውስጥ ያለው ችግር መፍትሄ እንዲያገኝ ጥረት ብታደርግ እንግዳ ወይንም ከመስመር የወጣ አይደለም። በጉዳዩ ሊኖራት የሚገባው ሚና ግን አሁን እንደምታደርገው ከአንዱ ወገን ጋር በማበር ሌላኛውን ለማጥፋት መሽለልና መፎከር ሳይሆን አለመግባባቱ ሠላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ ለማንም ሳያዳሉና ሳይወግኑ በቅን ልቦና መስራት ነው። ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ችግር መፈታት አወንታዊ አስተዋፅዖ ልታበረክት የምትችለውና የራሷንም ብሄራዊ ደህንነት የምትከላከለው ከአንዱ ወገን ጋር በማበር ሌላኛውን ወገን ጠላቷ በማድረግ ሳይሆን ከሁሉም ተጻራሪ ወገኖች ጋር ሠላማዊ ግንኙነትን በመፍጠር ነው። በአሁኑ ሠዓት ኢትዮጵያ እየወሰደች ያለችው እርምጃ የሶማሊያን ችግር ለመፍታት የሚረዳና የራሷንም ብሄራዊ ደህንነት የሚያስጠብቅ ሳይሆን ወደ ተቃራኒው ጎዳና የሚያመራ ነው። ኢትዮጵያ የሶማሊያን እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ጠላት በማድረግ እንዴት ነው ራሷን ከኦጋዴንም ሆነ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባራት ወይንም ኢትዮጵያን ለማናጋት የሚፈልጉ ከሚባሉት የውጭ ሃይላት ልትከላከል የምትችለው? ኢትዮጵያ የሶማሊያን እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት በጠላትነት በመፈረጇ ህብረቱ ከኦጋዴንና ከኦሮሞ ነፃነት ግንባራት ጋር ትብብርን በመፍጠር እንዲጠናከሩ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያን ለማናጋት የሚፈልጉ የውጭ ሃይላት ካሉም ለእነዚህ ኃይላት የመግቢያ ቀዳዳ የሚፈጥር ነው። ይህም የኢትዮጵያን ብሄራዊ ደህንነት የሚያስከብር ሳይሆን አደጋ ላይ የሚጥል እርምጃ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት የሶማሊያን ድንበር ጥሶ የገባበት ምክንያት የሃገሪቱን ብሄራዊ ደህንነት ለመጠበቅ ነው የሚል እምነት የለኝም። ዋነኛው ምክንያት መንግስት እንደ አሜሪካና ኢንግላንድ ባሉ መስቀለኛ ሀገሮች ዘንድ ያለውን ድጋፍ በማጠናከር የራሱን እድሜ ለማራዘም ሲል የተወሰደ እርምጃ ነው። መንግስት በግንቦቱ ምርጫ ያልጠበቀው አይነት ሽንፈት ከደረሰበትና አሸናፊዎቹን አስሮ ስልጣኑን በጉልበቱ ከያዘ ወዲህ በማዕራቡ አለም ዘንድ ልክ እንደ ዚንባቡዌው ሙጋቤ እንዳይተፋ አንቅቦ የያዘው በሶማሊያ ውስጥ ያለው የእርስ በርስ ግጭት እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቀዋል። መንግስት በአሁኑ ሰዓት ካርዶቹ በሙሉ አልቀው የቀረው ይሄው የሶማሊያ ጉዳይ ብቻ ነው። ሶማሊያ ውስጥ አንድ ጠንካራ መንግስት ባለመኖሩ ለሽብርተኞች መጠለያ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት በምዕራቡ አለም በተለይ በአሜሪካና በእንግሊዝ ዘንድ አለ። ምንም እንኳን ስለ ሶማሊያ የሚያውቁ በርካታ ግለሰቦችና የግብረ ሰናይ ማህበራት በሶማሊያ ውስጥ አልቃዒዳ ምንም ቦታ እንደሌለው አበክረው ቢያስረዱም ሰሚ ሊያገኙ አልቻሉም። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ኢትዮጵያ የምታሰራጨው ጭብጥ የሌለው የሽብር ቅስቀሳ እንደሆነ ለመለስ መንግስት አዲስ አበባን ያስለከበው ኸርማን ኮህን ሳይቀር መስክሯል።

ይህ የኢትዮጵያ መንግስት እየወሰደ ያለው እርምጃ ለጊዜው ስልጣኑን ለማቆየት የሚያስችለው ብልሃት መስሎ ቢታይም የኃላ ኃላ ግን ሊያስከትለው የሚችለው መዘዝ ለሃገሪቱ ብሄራዊ ደህንነት በጣም አደገኛ ሊሆን የሚችል ስለሆነ በአሁኑ ሠዓት የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ ሊቃወመው የሚገባው ሌላ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስትን ህገ ወጥ ጣልቃ ገብነት ነው እላለሁ።
አላሁ ዓለም!